# ነፋስ ሰውን ነዳው!



ገዳዩ ጨፍጫፊው ደም አፍሳሹ ብሎ፣
ትናንትና ማታ ሲጮህበት አድሮ፣
አቀፈና ሳመው ዛሬ አብዩ ብሎ!

አጥንቱ ውልክፉ የዛሬ ዘመን ሰው፣
ቀጥ ብሎ እማይቆም እንደ ሊጥ ልምሾ ነው፡፡

እስተ ቀራኒዮ ብሎ ማዩ ሁሉ፣
ሲሶ መንገድ ሳይደርስ ይሰበራል ቃሉ፡፡

የሰው የበግ መንጋን ምንድን ይለያቸው፣
አሳራጅ እረኛ እኩል ተነዳቸው?

ይብላኝ ለሞተ እንጅ ቋሚንስ ደልቶታል፣
ገዳዩ ሲዘፍን እስክስታ ያወርዳል፡፡

ላባ የሚከብደው የነፋስ ሽውታ፣
ምን ያህል ቢቀለው የሰውነት ገላ፣
አንስቶ አንሳፈፈው እንደ በጋ ትቢያ!

ጣምራ እጅ አያነሳው ሲባል የነበረው፣
የቀጣፊ ትንፋሽ ሲጠርገው አየነው፡፡

እየቀላቀለ ነፋስ ስልነዳው፣
ከባድና ቀላል እኩል ሆነ ዋጋው፡፡

የዚህ ዘመን ነፋስ ከዛር የከፋ ነው፣
እንኳን ገለባውን አለቱን አነሳው፡፡

ታጋዩ በሰለ አፈራ ስንለው፣
ትል የወጋው ዱባ ክፍት ሆኖ አገኘነው፡፡

በአልፎ ሃጂ ነፋስ የተወሰደ ሰው፣
ሰማዩ ሲሰክን ስካሩ ሲለቀው፣
በየ ቁጥቋጦው ሥር ወድቆ እሚገኝ ነው፣
ብርሃን ሲነጋ ወጥቶ መመልከት ነው፡፡

እባክህ ነፋሱ እረፍ አደብ ግዛ፣
በሰማዕት መቃብር አረምን አትዝራ!

እባክህ መለኮት ለሰው ክብደት ስጠው፣
እንደ ገብስ ገለባ ነፋስ እንዳይጠርግው፡፡

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ህዳር ሰላሳ ሁለት ሺ አስራ ሁለት  ዓ.ም.